አፍሪካ ቲቪ

ከታላቁ ቁርአን
የመጨረሻዎቹ
‹‹የሶስቱ ክፍሎች››
ማብራሪያ
ዋና ዋቢ
ዙብደቱ ተፍሲር



# አፍሪካ አካዳሚ
# AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአቂዳ ትምህርት 2

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

## ሁለተኛው አለም አቀፍ የርቀት ትምህርት መሪ ቃል
## “ትክክለኛው ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው”

إِنَّ الدِّينَ عِندَ اللَّهِ الْإِسْلَامُ

“አላህ ዘንድ የተወደደው ሀይማኖት ኢስላም ብቻ ነው ፡፡”

ሁሉንም ሙስሊም የሚመለከቱ

የአፍሪካ አካዳሚ

የርቀት ትምህርት

1441 ሒጅሪያ/2020

- የአምስተኛው ቀን ትምህርት  በአላህ መፅሀፍት ማመን ነው፡፡
- የኢማን መሠረቶች

## 3. በመፃህፍት ማመን

ይህን የላቀ የእምነት ማዕዘን መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ በበርካታ የቁርዓን ኣያዎች አላህ ነግሮናል፤ እንዲሁም ነቢዩም ሰ.ዐ.ወ በሰፊው አስተምረዋል፡፡

# ቁርአን ምንድን ነው?

ቁርአን የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡፡

እሱን በማንበብ ብቻ እንኳን የአላህ (ሱ.ወ) አምልኮ ይገለፅበታል፡፡

እሱ ዘንድ ወርዶ ወደሱ ይመለሳል፡፡ በፊደሉም ሆነ በድምፅ ተናግሮታል፡፡

ቁርአን መልአኩ ጂብሪል ከአላህ (ሱ.ወ) ሰምቶት ከዚያም ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አድርሶታል፡፡

ቁርአን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሰማያዊ መፅሐፍት ሁሉ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ናቸው፡፡

- **የአሏህ ሱ.ወ ቅዱሳን መጽሃፍቶች ምንድናቸው?**

  ሁሉም የአሏህ ሱ.ወ ቃሎች ናቸው፡፡

- ተውራት፡- ተውራት አላህ ለሙሳ የሰጠው መፅሐፍ ነው፡፡
- ኢንጂል፡- ኢንጂል በመርየም ልጅ ኢሳ ላይ የወረደ መፅሐፍ ነው፡፡
- ዘቡር፡- ዘቡር በዳውድ ላይ የወረደ መፅሐፍ ነው፡፡
- **የሙሳ እና የኢብራሂም ሱሁፍ (ጽሁፍ)**
- ቁርአን፡- ቁርአን በነብዩ ሙሐመድ ሰ.ዐ.ወ ላይ የወረደ ሲሆን ከበፊቱ ለነበሩት መስካሪ የሁሉም የበላይ ፈራጅና ሁሉን ሰርዞ የሚተኻ መፅሐፍ ነው፡፡ መጨረሻ ላይ የወረደና ከሁሉም በላጭ ከሁሉም ይበልጥ የተሟላ መፅሐፍ ነው፡፡

## 16-ሀዲስን ትተን በቁርአን ብቻ መብቃቃት ይቻላልን?

አይቻልም፡፡ ምክንያቱም አላህ (ሱ.ወ) ራሱ ሀዲስን እንድንይዝ (መልዕክተኛው የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት፡፡ ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ፡፡) በማለት አዟልና፡፡

**ሀዲስ ደግሞ የቁርአን ማብራሪያ ነው፡፡ የኢስላም ህግጋቱም ሆነ ስርአት ዝርዝሩ ለምሳሌ:-የሶላትን አሰጋገድ ዝርዝረ ስርአቱን ይመስል ያለ ሐዲስ አይታወቅም፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አህመድና አቡ ዳውድ በዘገቡት ሐዲስ (አዋጅ! ቁርአንና መሰሉን ተሰጥቻለሁ፡፡ አዋጅ! አንዳንድ የጠገቡ ሰዎች በትራሳቸው ላይ ተደግፈው ይህን ቁርአን ብቻ ያዙ፡፡ እሱ ሀላል ያደረገላችሁን ብቻ ሐላል በሉ፡፡ ሐራም ያደረገባችሁንም ብቻ ሀራም በሉ ለማለት ይቀርባሉ) ብለዋል፡፡**

## የኢስላም ህግጋቱም ሆነ ስርአተ ዝርዝሩ ለምሳሌ ፡-

የሶላትን አሰጋገድ ዝርዝረ ስርአቱን ይመስል ያለ ሐዲስ አይታወቅም፡፡

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አህመድና አቡ ዳውድ በዘገቡት ሐዲስ (አዋጅ! ቁርአንና መሰሉን ተሰጥቻለሁ፡፡

አዋጅ! አንዳንድ የጠገቡ ሰዎች በትራሳቸው ላይ ተደግፈው ይህን ቁርአን ብቻ ያዙ፡፡

እሱ ሀላል ያደረገላችሁን ብቻ ሐላል በሉ፡፡

ሐራም ያደረገባችሁንም ብቻ ሀራም በሉ ለማለት ይቀርባሉ) ብለዋል፡፡

## ቁርኣንን በማንበብ የሚገኘው አጅር (ምንዳ)

የተከበረው ቁርኣን የአላህ ቃል ነው፡፡ ከንግግሮች ሁሉ ያለው ታላቅነት በፍጡራኑ ላይ ያለውን ታላቅነት ያህል ነው፡፡ ምላስ ከሚንቀሣቀስባቸዉ ነገሮች ሁሉ የሚበልጠው እሱን ማንበብ ነው፡፡ ቁርኣንን መማር ማስተማርና ማንበቡ ብዙ ትሩፋቶችና አያሌ ምንዳዎች አሉት፡፡

ከነዚህም ትሩፋቶች መካከል፡-

የማስተማሩን ምንዳ በተመለከተ:-

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ከሁላችሁም የሚበልጠው ቁርኣንን ተምሮ ያስተማረ ሰው ነው ብለዋል፡፡

## በቀንና በሌሊት መነበብ ያለበት አነስተኛው የቁርኣን አንቀፅ መጠን

የነቢዩ ነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች በየቀኑ ከቁርኣን የሆነ ልክ ያነቡ ነበር፡፡ ሆኖም ሙሉ ቁርኣንን ከሰባት ቀን ባነሰ ጊዜ ውስጥ መጨረስ የብዙዎቹ ተግባር አልነበረም፡፡ ብሎም ከሶስት ቀን ባነሰ ሙሉዉን ማንበብ መከልከሉ ከነቢያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ተዘግቧል፡፡ ስለዚህ ዉድ ወንድሜ ሆይ! ቁርኣንን በማንበብ ጊዜህን በመልካም ነገር አሳልፍ፡፡

*** አደራ፡-** በየቀኑ ምንም ከባድ ችግር ቢገጥምህ እንኳን የማትተወው የተወሰነ መጠን ከቁርኣን የማንበብ ልምድ /ዉርድ/ ይኑርህ፡፡ በብዛት ተጀምሮ ከሚቋረጥ አነስተኛ ሆኖ የሚቀጥል ነገር ይሻላል፡፡ ከዉርድህ ብትዘናጋ ወይም ብትተኛና ቢያልፍህ በበነጋው ቀዷ አውጣው፡፡ ይህን በተመለከተ ነብዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ከዉርዱ ወይም ከሌላ ነገሩ የተኛና ከሱብሂ እስከ ዙህር ድረስ ባለው ሰዐት ቀዷ ማውጣት የቻለ ሰው በሌሊት እንዳነበበው /እንደሰራው/ይቆጠርለታል) ብለዋል፡፡